# መድረክ ፤ ወይስ መድረቅ?

አንቺ ምን አለብሽ ፤ ሁለት አባት አለሽ
አንዱ ቢሞትብሽ ፤ ባንዱ ትምያለሽ
ህዝቡን ላትከጂ ፤ በያድባሩ ምለሽ
መሽቶ እንኳን ሳይነጋ ፤ በክህደት ተኩለሽ
በጎጠኛ ጀልባ ፤ መኮፈስ መምነሽነሽ
ቀን ህዝባዊ ሆኖ ፤ ከወያኔ ሲመሽ ።

ሁለት ዛፍ መውጣት ፤ ሁለት እግር ይዞ
ሀሰትና ክህደት ፤ በስውር አርግዞ
ሕዝብን እየከዱ ፤ የጨለማ ጉዞ
ባስመሳይ ታጋዮች ፤ ትግሉ ተመርዞ
ጠረኑን አከፉት ፤ ግምኛ መርቅዞ ።

አንደኛው ሲሰበር ፤ ባንደኛው ተንጠልጠል
ልብ እየዋለለ ፤ መሥዋት አትክፈል
በፈሪ መፈክር ፤ ህዝብን መከፋፈል
ግፍ አይታክታችሁ ፤ ደጋግሞ መበደል ።

ቀኝ እጅ የወያኔ ፤ ግራው ተቃዋሚ
አንደኛው ላንደኛው ፤ ሆነው አስታማሚ
ባላንጣ ነን ሲሉ ፤ ይገርማል ለሰሚ
በተበላ እቁብ ፤ ዘወትር አዝጋሚ
የሰለቸ ነገር ፤ ትግልን አድካሚ ።

ባንዳና ከሀዲ ፤ ውዥንብር ፈጣሪ
የሀሰት ማደሪያ ፤ ትውልድ አሳፋሪ
የወያኔ አገልጋይ ፤ የጎጠኞች ጋሪ
ማፈሪያዎች ናችሁ ፤ ትግልን ቀባሪ
አላደላችሁም ልትሆኑ ፤ አገር አኩሪ ።

ገዳይ ቢዘገይም ፤ ሟች ይገሰግሳል
በሸፍጥ የገነቡት ፤ አይቆይም ይፈርሳል
ህዝብን እንደረሳ ፤ በተራው ይረሳል
በጥቁር ታሪኩ ፤ ዘወትር ይወሳል
ነገ እናየዋለን ፤ አይቀርም ይደርሳል ።

ታሪክን ከረሳ ፤ ሁሌም ካልተማረ
በህዝብ ላይ ፊቱን ፤ ደጋግሞ ካዞረ
የወዳጅ የዘመድ ፤ አንጀት እያረረ
ቢፈለጥ ፤ ቢከተፍ ፤ እየተመተረ
ሀዘን አይገባም ፤ ተረስቶ ለቀረ
በትግል አጋሩ ፤ ጦር ለወረወረ ።

መድረክ አሉት ስሙን ፤ እንዳይባል መድረቅ
አይንን በጨው አጥቦ ፤ ባደባባይ መስረቅ
ዘርፎ መመፃደቅ ፤ ቀረና መደበቅ
ዘመነ ግርንቢጥ ፤ የሰው ልብ ማውለቅ ።

ከሰላማዊት. አ